

# የዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ አጭር የህይወት ታሪክ።

ከአባቱ አቶ ዳባሳይ ካሕሳይና ከናቱ ወይዘሮ መሕረታ ዓዶዑማር በ 1933 ዓ.ም. በኢሮብ ወረዳ ዋና ከተማ በዓሊተና ተወለደ። ዕድሜው ለትምህርት እንደደረሰ እዛው ዓሊተና ከነበረው የካቶሊክ ቤተክርስትያን በወቅቱ ለልጆች ይሰጥ የነበረውን ትምህርተ ክርስቶስና ፊደል መቁጠርና ማንበብ ተማረ። ዓሊትና የነበረው የቆየው ታሪካዊው የካቶሊክ ትምህርት ቤት፣ ከጣልያን ሁለተኛ ጊዜ ወረራ በኋላ ተዘግቶ ስለነበረ፣ የመማር ከፈተኛ ፍላጎት የነበርው ተስፋይ ትምህርት መቀጠል አልቻለም። ምክንያቱም በውቅቱ መደበኛ ትምህርት የሚሰጥ የነበረው ዓዲግራት በነበረው የካቶሊክ ትምህርት ቤትና በመንግስት ደረጃ ደግሞ አግ ኣዚ መልስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ብቻ ስለነበ፣ ዓዲግራትም ከዓሊተና ሩቅ ስለነበረ፣ ወላጆቹ ገንዘብ ከፍለው እንዳያስተምሩት ደግሞ ድሆች ስለነበሩ ነበር።

ከፍተኛ የመማር ፍላጎት የነበረው የተስፋይ ምኞት ግን መና ሆኖ አልቀረም። አስመራ ሲኖሩ የነበሩ የአያቱ (የናቱ እናት እህት፣ እናቴ ጋቢሩ ዓሊ) የሚባሉ ሞኖክሴ ከአስመራ ቤተሰብ ለመጠየቅ መጥተው የተስፋይ ለትምህርት የነበረ ጉግት ከእህታቸው ሰሙና ወደ አስመራ ከመመለሳቸ በፊት ይዘዉት ወደ ዓዲግራት በመሄድ አስፈላጊውን ልብስ ገዝተው፣ የዓመት ክፍያውን ከፍለው አዲግራት የነበረው የካቶሊክ አዳሪ ትምህርትቤ አስገቡትና ህልሙ እውን ሆነ፣ እስከ 8 ኛ ክፍልም ትምህርቱን በአዳሪነት እዛው ዓዲግራት ካቶሊክ ትምህርት ቤት ቀጠለ። 9 ኛ ክፍል መቐለ በሚገኘው አጼ ዮሃንስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማረ። 10 ኛ ክፍል እንደገና ወደ ዓዲግራት የካቶሊክ ትምህርትቤ ተምልሶ ተማረ።

10 ኛ ክፍል እንደ ጨረሰ ለከፈተኛ የፊሎዞፊና ቲዮሎጂ ትምህርት ወደ ጣሊያን (ቫቲካን) ተለከ። ገና ከልጅነቱ ጀምሮ መመራመር የሚወድ የነበረ ተስፋይ የፍልስፍና ትምህርቱን በ Urbaniana Universy መማር ጀመረ። ከአርስቶትል እስከ ዘመናዊ ፈላስፋዎች ፍልስፍና በሚገባ ተከታትሎ በመጨረስ በፍልስፍና ታሪክ የዶክተረይት መዓርጉን በከፍተኛ ወጤት አገኘ። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተስፋይን ወደ ቫቲካን ስትልከው ዓላማዋ ተስፋይ የተማረ የካቶሊክ ካህን እንዲሆን ነበረ። ተስፋይ ግን ከዚህ የተለየ አጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝቦች ከመስፍናዊ አገዛዝ ነጻ የማውጣት ዓላማ በውስጡ ይዞ ስለነበረ ክህነትን ወይድ ብሎ ሁኔታዎችን በሀገር ቤት ሆኖ ለመከታተለ የዶክተረይት ድግሪውን እንዳገኘ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በህዝቡ መካከል እየኖረ ሁኔታውን ይበልጥ ለማጥናትና እንዴት ትግሉን እንጀምረው በሚለው ላይ ለመስራት ወሰነ።

ወደ ሀገር ቤት እንደተመለሰ በስራ ፍለጋ የሚረዳው ቤተሰብ ሆነ ጓደኛ ባይኖረውም ዶክተር ተስፋይ ከፍተኛ ዕውቀትና ችሎታ ስለነበርው ስራ ለማግኘት ብዙ አልተቸገረም። በወቅቱ በተለያዩ ሚንስቴር መስራቤቶች ኤክስፐርቶች ይፈለጉ ስለነበረ

የተለያዩ መስሪያቤቶች ለስራ ፈላጊዎች የሚያውጡዋቸው ማስታወቂያዎች በጋዜጦች፣ በሬዲዮና በተልቪዥን ይተላለፉ ስለነበረ፣ ዶክተር ተስፋይ የሚፈልገውን ስራ በማስታወቂያዎቹ አማካይነት ይከተተል ጀመረ። አገር ቤት እንደተመለሰ ብዙ ሳይቆይ በማስታወቂያ ሚንስተር በስነጽሁፍ ክፍል፣ በተመራማሪነትና ፕላኒግ የሚሰራ ሰራተኛ እንደሚፈለግ የሚገልጽ ማስታወቂያ ተመለከተና በቀጥታ ለስራው ማመልከቻ አስገባ። በማመልከቻው መሰረት ለቅጥር ምርመራ ሲደረግ መርማሪዎቹ የዶክተር ተስፋይን ብቃት በቀላሉ ለማየት ስለቻሉ በቀጥታ ቀጠሩትና በማስታወቂያ ሚንስተር፣ በስነጽሁፍ ክፍል በተማራማሪነት ስራ ጀመረ። በዚህ ስራው እያለ ከተለያዩ ሚንስተር መስሪያቤቶች ሰራተኞች፣ የተለያዩ ዲፕሎማቶች፣ ምሁራን፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ በተለይ በውቅቱ የተማሪው እንቅስቃሴ ሲመሩ ከነበሩ ታዋቂ ተማሪዎች ጋራ ለመተዋውቅና የረጅም ጊዜ ዕቅዱን ወደ ተግባር ለመለወጥ ጥሩ ዕድል አገኘ።

የስርዓቱም ቢሮክራሲ በሚገባ ለማጥናትና ለማወቅም ቻለ። ከዚህ በተጨማሪም ማታ ማታ በአባዲና ኮለጅ መኮነኖችን ፍልስፍና ያስተምር ስለነበረ ከተለያዩ ወታደራዊ መኮነኖችም ለመተዋወቅና በኋላ በደርግ የተመታው ክፍል በራሱ በደርግ ውስጥ እንዲፈጠር የተለያዩ ወታደራዊ መኮነኖች ከሰራዊቱ ለወድፊቱ ትግል ለመመልመል ጥሩ ዕድል አገኘ። በዚህ የስራ ወቅቱ ከሌሎች ተራማጅ ምሁራንና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጋራ በመሆን ዶክተር ተስፋይ ከፍተኛ ቱክረት ሰጥቶት ይሰራ የነበረው ከተማሪው እንቅስቃሴ ከተወለዱት የፖለቲካ ድርጅቶች አንዱ የሆነው ሲመሰረት የኢትዮጵያ ህዝቦች የአርነት ድርጅት (ኢህአድ) በኋላ ከ 1967 ነሓሴ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ አቢዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ለመመስረት የሚደረግ የነበረውን ዝግጅት ጀመረ።

በ 1964 ዓ.ም. መጀመሪያ በሀገር ቤት በነበረው የተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ስለ ፖለቲካ ድርጅት ኢህአድ መመስረት ስምምነት ከተደረስ በኋላ ለሚመሰረተው የፖለቲካ ድርጅት ከፍተኛ አስተዋጽ ኦ ሊያደርጉ የሚችሉ በውጭ በተለይ በአውሮጳና በአመሪካ የነበሩትን የተማሪዎች ማህበራት በዚህ ድርጅት ዙሪያ ለማሰባሰብ ሲደረግ የነበረውን ስራ ለመርዳት ዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ ትምህርትን አሳቦ ወደ አውሮጳ ሱዊዘርላንድ ተመለሰ። ለሁለተኛ ድግሪው የሚማረው ትምህርት እንዳለ ሆኖ ዋናው ስራው ግን በኢውሮጳና አመሪካ በተለያዩ ሀገራትና እስቴይትስ የነበሩ የተማሪዎች ማህበራት በፈደረሽን ማደራጀትና ማገናኘት ቀጥሎም ከነዚህ ማህበራት ለሚመሰረተው የፖለቲካ ድርጅት አባላት መመልመል ስራን ከሌሎች ጓዶቹ ጋራ በሚገባ አከናወነ።

በውጭ በተለያዩ ሀገራት የነበሩ የተማሪዎች ማህበራት ወደ አውሮጳ የተማሪዎች ማህበርና ወደ መላው አመሪካ የተማሪዎች ማህበር እንዲያድጉ በተደረገው ትግል የዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ አስተዋጽኦ ከፈተኛ ነበር። እንዲሁም ከነዚህ ማህበራት የኢህአድ አባላትና ደጋፊዎች በመመልመሉ ስራም ዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ ከፈተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ከተማሪው እንቅስቃሴ በ 1964 በጀርመን (በርሊን) የተወለደው ኢህአድ መስራች ጉባኤ በማዘጋጀትና በመምራትም ከፈተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱትና በጉባኤው የድርጅቱ አመራር ሆነው ከተመረጡት 9 ኙ አመራሮችም አንዱ ሆኖም ተመረጠ።

ኢህአድ ከተመሰረተ በኋላ ለሁለተኛ ድግሪው እየሰራ እያለ የ 1966 ቱ ህዝባዊ ኢብዮት ተቀጣጥሎ የአፄ ኃይለስለኣሴ ስርዓት መንገዳገድ በጀመረበት ወቅት ህዝባዊ አቢዮቱን ሀገር ቤት ሆኖ መምራት የግድ ይል ስለነበረ ዶክተር ተስፋይ የሁለተኛ ድግሪው ትምህርቱን አቋርጦ ወደ ሀገርቤት ተመለሰ።

በስዊዘርላንድ ትምህርቱን እየተከታተለ እያለ በስዊስ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት ልጅ ሚካኤል እምሩ ዶክተር ተስፋይ ጋር ጥሩ ትውውቅና ቅርበት ስለነበራቸው ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው ልጅ እንዳልካቸው መኮነን በንጉሱ ትዕዛዝ ጠቅላይ ሚንስተር የነበሩትን አቶ አክሊሉ ሃብተወልድ እንዲተኩ በተደረገበት ወቅት የልጅ እንዳልካቸው ቦታ ተክተው ይሰሩ ስለነበርና የዶክተር ተስፋይ ወደ ሀገር ቤት መግባት ያውቁ ስለነበረ ዶክተር ተስፋይን አስጠርተው የመሬት ይዞታ ሚንስተር ሆኖ እንዲሰራ ጠየቁት። ዶክተር ተስፋይ የራሱ የተለየ ዕቅድ ስለነበረው ለተከበሩ ልጅ ሚካኤል የሚንስተሩን ቦታ እንደማይቀበለው በትህትና አስረድቶ፣ በትግራይ በመሬት ይዞታ ሃላፊነት ከተመደ ግን ለመስራት ዝግጁ መሆኑ ነገራቸው። ልጅ ሚካኤልም ጥያቄውን ተቀብለዉት በትግራይ ጠቅላይ ግዛት የመሬት ይዞታ ሃላፊ ሆኖ እንዲሰራ መደቡት።

ግልጽ ስራው የመሬት ይዞታ ሃላፊ ሆኖ መስራት ሆኖ ተጨማሪ የህቡእ የኢህአድ ስራውን በግልጽ ስራው ሽፋን ማቀላጠፍ ሆነ። ከትግራይ በመነሳት መላው ሀገሪቷ ውስጥ በተለያየ ሰበብ እየተንቀሳቀሰ ከሌሎች ጓዶቹ ጋራ እየተገናኘ የኢህ አድ መዋቅር በሀገሪቷ ሁሉ እንዲዋቀር ከፊተኛ አስተዋጽኦ አበረከተ።

በተለይ ደግሞ በበርሊኑ የጉባኤ ወሳኔ መሰረት በውጭ በሶሪያ በ PLO ሰልጥኖ ትጥቅ ትግል ለመጀመር ትግራይ (ዓሲምባ) እንዲገባ ተወስኖ ለነበረው ትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን ቦታ በዓዲ ኢሮብ ሲያዘጋጁ ለነበሩ ጓዶቹ በቅርበት መመሪያ በመስጠትም ሰራ። በ 1967 መጋቢት 23 ትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን ወደ ዓሲምባ ከገባ በኋላም ከቡድኑ ጋራ በመገናኘት፣ ትጥቅ ትግሉና የከተማው የህቡእ ትግል በማገናኘት ሰራ።

በዚህ ሁኔታና ስራው ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላም በልጅ ሚካኤል እምሩ በተመደበበት የመሬት ይዞታ መስሪያቤት የመንግስት ደሞዝ እየወሰደ፣ የመንግስት ነበረት ሁሉ እንደልቡ እየተጠቀመ በመሬት ይዞታ ስራ ሽፋን በዋናነት የኢህ አድን ስራ እየሰራ እስከ 1967 መጨረሻ አከባቢ ቆየ። በ 1967 ክረምት ላይ ከትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን 8 የሚሆኑት አንድ ላይ ከድተው ወደ ደርግ ከገቡ በኋላ፣ እነዛ ከድተው የገቡት ዶክተር ተስፋይ ደበሳይን በተለያየ ጊዜ ዓሲምባ ድረስ እየሄደ ከብርሃነመስቀል ረዳ (የትጥቅ ትግል ጀማሪ ቡድን መሪና የኢህ አድ አመራር አባል የነበረ) ጋራ በየጊዜው ሲያደርገው የነበረ ግኑኝነት ያውቁ ስለነበረ የመሬት ይዞታ ስራው ሽፋኑን ተጋለጠ፣ ከዛች ዕለት ጀምሮም የመሬት ይዞታ ስራውን አቁሞ ህቡእ ኣንዲገባ ተገደደ።

ከ 1967 መጨረሻ እስከ ተሰዋበት መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም. በህቡእ ኢህ አፓን የመምራት ስራውን አዲስ አበባን ማእከሉ አድርጎ ከጓዶቹ ጋራ በመሆን ሲሰራ ቆየ። ህቡእ ከገባባት ዕለት ጀምሮ ፋሽስታዊ ደርግ ብዙ ክትትል ቢያደርግበትም ዱካዉን ለማግኘት

አልቻለም ነበር። በ 1968 መጨረሻዎቹ አከባቢ በኢህ አፓ ላይ በደርግ የተጀመረው የማጥፋት ዘመቻና በራሱ በድርጅቱ አመራር ወስጥ የተጀመረው የሃሳብ ልዩነት የዶክተር ተስፋይና መሰሎቹ የኢህ አፓ አመራር የህቡእ ኑሮና ስራ እጅጉን ያወሳሰቡትና አስቸጋሪ የደርጉት ጀመረ።

በ 1969 ደርግ ቀይ ሽብር በሚል በኢህ አፓ ላይ ግልጽ የማጥፋት ዘመቻ ካወጀ በኋላ ውስብስብ የነበረው ሁኔታ የኢህአፓ አመራር ሊቆጣጠረው ከምችለው በላይ ሆነ። እጅግ ብዙ የኢህ አፓ አባልት፣ የወጣት ክንፉ የኢህ አወሊ አባልት፣ ከኢህ አፓ ጋር ግኑኝነት ያልነበራቸው ንጹሃን ኢትዮጵያዊያን ባጭር ቀናት ውስጥት በዚህ ቀይ ሽብር ዘመቻ በፋሽስቱ ደርግ ታጨዱ። ከኢህ አፓ አመራርም በርካቶቹ በዚህ ቀይ ሽብር ተሰዉ።

በዚህ የቀይ ሽብር ዘመቻ በተጧጧፈት ወቅት ዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ አዲስ አበባ ሆኖ ይህን እልቂት ይመለከት ነበር። ራሱን ማዳን ቢፈልግ ደግሞ ራሱን ለማዳን ዕድል ነበረው። ግን ይህን አልመረጠም፣ በተቻለው አቅም ለራሱ ህይወት ሳይሳሳ ማዳን የምችለውን ያህል ጓዶቹን ከእልቂቱ ለመታደግ መሯሯጠን መረጠ።

በዛ ዘመቻው እጂግ ከባድ በነበረበት ዕለታትም በርካታ አባላትን ወደተለያዩ የገጠር ክፍሎች እንዲወጡና እንዲድኑ አስደረገ። በዛች ቀውጢ ወቅት በራሱ ላይ ሲደረግበት የነበረውን ክትትል ለማምለጥ እዛው አዲስ አበባ ከቦታ ቦታ በመቀያየር እየተንቀሳቀሰ እያለ በመጨረሻ በአምባሳደር ቲያትር አጠገብ ካለው በውቅቱ የኪዳነ በየነ ህንጻ እየተባለ ሲጠራ ከነበረው ህንጻ ከአንድ በሪሁን ማሪየ ከሚባል ጓዱ ጋራ ሲገቡ ሲከታተሉዋቸው በነበሩ የደርግ ገዳዮች ጓድ ማርየ ውዲያ ሲገደል ዶክተር ተስፋይ ቆሰለ። መቁሰሉን የተመለከቱ የደርግ ገዳዮች እጅህን ስጥ ሲሉት ለፋሽስቶች እጄን አልሰጥም፣ ብሎ ደሙ እየፈሰሰ በሩጫ ደረጃዎቹን በመውጣት ከህንጻው 6 ኛ ፎቅ ተወርውሮ በመሬት ላይ በመፈጥፈጥ መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም. ተሰዋ።

ዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ፣ ብዙ የማይናገር፣ አድማጭ፣ ሊታይ ሊታይ የማይል፣ ማንቱን በቀላሉ ልታውቀ የማትችል፣ አመራርን ራሱ አር አያ ሆኖ የሚሰጥ፣ ከራሱ በፊት የሚመራቸው የነበረ አባላትን የሚያስቀድም የተግባር ሰው መኖሩ ስለ ጓዶቹ የሚያውቀው የነበረውን ሚስጥር ላለመስጠት ወድ ህይወቱን ቤዛ ጓዶቹ የሰጠ ታላቅ ምሁርና ለኢትዮጵያ እጂግ በጣም ሲያስፈልጉዋት ከነበሩ በውቅቱ ከነበሩ ምሁራን አንዱ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ክበር ለጓድ ተስፋይና ላመኑበት ዓላማ ውድ ህይወታቸውን ለሰጡ ሰማዕታት በሙሉ!!!

በየነ ገብራይ፣ ደንማርክ።

አቶ ክፍሉ ታደሰ፣ የቀድሞ የኢህ አፓ አመራር አባል ስለ ዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ በመጽሃፋቸ የሰጡት ምስክርነት፣

አንዳንድ የተነሱ ጥያቄዎችን ሊመልስ ይችላል ብዬ ስላመንኩ ከዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ ጋራ ከምስረታው ጀምሮ እስከ ዕለተ ህልፈቱ አብሮ በኢህ አፓ ፖሊት ቢሮ አብሮ የሰራ አቶ ክፍሉ ታደሰ በያትውልድ ቅጽ 2 ገጽ 330—332 የኢህ አፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብጥር በሚል ን ኡስ ርእስ ስለ አጠቃላይ ኮሚቴ ካሰፈረው ስለ ዶክተር ተስፋይ ዳባሳይ የሰጠውን ምስክርነቱን ብቻ መዝገቤ ለማስፈር ፈለኩ። የማእከላዊ ኮሚቴው የትምህርት ደርጃ ሲያስቀምጥ፣ እጠቅሳለሁ፣ “ተስፋዬ ደበሣይ የዶክተረይት ዲግሪ የነበረውና በ 1966 ቱ አቢዮት ሲቀሰቅሰም ለሁለትኛ የዶክተረይት እየሰራ የቆየ ምሁር ነበር።”

ስለ ማእከላዊ ኮሚቴው አባላት የትውልድ ሁኔታ በሚገልጽበት የመጨርሻ ክፍል ዶክተር ተስፋይ ዳባሳይን እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፣ እጠቅሳለሁ፣ “የፍልስፍና ተማሪ የነበረው ተስፋዬ ደበሣይ ከማርክሳዊ ፍልስፍና ጋራ የተዋወቀው ፍትሃዊ ስርዓተ ማህበር የሚመሰረትበትን ሁኔታ ለማወቅ ጥረት ያደርግ በነበረበት ጊዜ ነው። ትክክለኛውን ፍልስፍና ለማግኘት ተስፋዬ ባደረገው የምርምር ጉዞ ከተምኔታዊ ሶሺያልስቶቹ ከነቅዱስ ሳይመን ተነስቶ የእነ ዣን ዣክ ሩሶን፣ የአማኑ ኤል ካንትና የመሳሳስሉትን ታላላቅ ፈላስፎች ስራዎች መርምሮ በመጨረሻ የመርክስን ስራዎች እስኪያነብ ድረስ በየተራ የሁሉም ደቀ መዝሙር ሆኖ ቆይቷል።” ይለዋል።

ስለ ኢህ አፓ አመራር ምን ዓይነት ሰዎች ነበሩ፣ የብሄረስብ ስብጥራቸው ምን ይመስል ነበር፣ የትምህርትና የዕድሜ ደርጃቸው ምን ይመስል ነበር፣ ከየተኛ የህብረተሰብ ክፍል የተወለዱ ነበሩ፣ አጠቃላይ ይትግል ኑሮዋቸው ምን ይመስል ነበር ከአቶ ክፍሉ ያትውልድ ቅጽ 2 ከገጽ 330—332 ላይ ተገኙታለችሁና ስለ አመራሩ በጣም ጥሩ ስዕል ስለሚሰጥ አንብቡት።

http://www.ethiopanorama.com